**Hessisches Ministerium für Soziales und Integration**

HESSEN

**ማሳሰቢያ፣ ኣዲስ መረጃ!** **የ 23.3.2020 ሁኔታ**

የፌደራልና ክልል ኣስተዳደሮች፣ በ 12. 03 የተደረሱትን የማህበረሰባዊ ግንኙነት ቁጥጥር የማጥበቅ መሪ ሓሳቦች ማጠናከር በሚመለከት ጉዳይ ስምምነት ላይ ደርሷል። ስምምነቱ በሄሰንም ተተግባሪነት ይኖሯል።

1. ነዋሪዎች ከገዛ ራስ ቤተ ሰባቸው ውጭ ኣልፈው ከሌሎች ሰዎች የሚያደርጉት ግንኙነት በተቻል መጠን እንዲቀንሱት ይጠየቃሉ።

2. በማሕበራዊ ግንኙነት በተቻለ መጠን በ 1 ቁጥር ከተጠቀሱት ግለ ሰቦች ውጭ፣ ቢያንስ 1,5 ሜትር ርቀው እንዲለዩ። .

3. ማሕበራዊ ተጠቃሚነት ባለበት ቦታ፣ ኣብሮ ክማይኖርና፣ የቤተሰብ ኣባል ካልሆነ ከኣንድ ሰው ብቻ መገናት ይፈቀዳል።.

4. ወደ ሥራ ለመሄድ፣ ኣስቸኳይ እርዳታ ለመስጠት፣ ወደ ገበያ ለመሄድ፣ ወደ ሃኪም ቤት ለመሄድ፣ ባስፈላጊ ስብሰባዎች ለመገናት፣ ቀጠሮ ለመጠበቅ፣ ፈተና ለመፈተን፣ ሌሎችን ለመርዳት፣ የግል ስፖርትና የኣካል እንቅስቃሴ ለማድረግ ኣዲስ ኣየር ለማግኘት ከቤት መውጣት ይፈቀዳል።

5. በሕዝባዊ መገናኛ ቦታዎች፣ መኖሪያ ቤቶችና የግል ሕንጻዎች ተሰብስቦ መዝናናት ኣገራችን ኣጋጥሟት ካለው ሁኔታ ኣንጻር ሲታይ ተቀባይነት የለውም። የግንኙነት ማዕቀቦች ጥሰቶች በሥርዓት ጥበቃ ባለሥልጣኖችና ፖሊስ (Ordnungsbehörden und der Polize) ቁጥጥር ሥር ሁነው እንዲጠበቁ መደረግ ኣለባቸው።

6. የምግብ ቤቶች ይዘጋሉ። ከዚሁ በተለይ፣ ወደ ደምበኛ የሚላኩና ሊወሰዱ የሚቻሉ ሆነው ወደ ቤት ተወስደው የሚበሉ ምግቦች ይፈቀዳሉ።

7. የኣካል እንክብካቤ፣ የጸጉር ሞያ፣ የቁንጅና ሳሎኖች፣ የማሳዥ ቤቶች፣ የመንቀሻ ሳሎኖችና ተመሳሳይ ኣገግሎት ሰጪዎች ይዘጋሉ። በዚሁ የሥነ ኣካል ዘርፍ የግድ ኣስፈልዓጊ ጉዳዮች ስለሚኖሩ፣ ሕክምናዊ ኣስፈላጊነት ያላቸው ክፍት እንዲሆኑ ይፈቀዳል።

8. በየተቋሙ፣ በተለየም ብዙ ሰዎች በሚንቀሳቀሱባቸው ተቋሞች፣ የጽዳት መመሪያዎች መጠበቅ፣ የሰራተኞቹና የጎብኚዎቹ ደህንነት መጠበቅ የግድ ኣስፈላጊ ይሆናል።.

9. ይህ እርምጃ ቢያንስ ለሁለት ሳምንት ያህል ተተግባሪነት ይኖሯል።.

በተጨማሪ በሚከተለው ሆት ላይን፣ ከጠዋት 8 ሰዓት እስከ ማታ 20 ሰዓት በነጻ መረጃ ያገኛሉ: **0800 555 4 666**
ከዚህም በተጨናሪ በ **APP HessenWARN** እና በ **www.Hessen.de** ድረ ገጽ መረጃ ያገኛሉ።